# ጊዜ እሯጩና ሚዛኑ

ከማተቤ መለሰ ተሰማ

ጊዜ እንደዋዛ አለፈ፣ እሮጠ፣ በረረ፣
የኢተዮጵያ ህዝብ፡ እንደቦቆሎ ተሸፍኖ፡ እንዳረረ።
የሽብሪ፣የነብዮ፣የከበቡሽ፡ ደም እየተጣራ፣
እንሆ ተቆጠረ፡ ሰባት አመት፡ ምንም ነገር ሳነሰራ።
ጊዜማ ምን ገዶት፡ አያ ዞሮ ሳያይ ከነፈ፣
ወገንን፡ እንደቅጠል፡ እያረገፈ።
እኛ ግን፡ ወደፊት ላንራመድ፡ ቆመናል ካንድ ቦታ፣
እርስ በእርስ ስንጎሻሸም፡ በነገር ዱላ ስንማታ።
ጠላት አበጠ ተኮፈሰ፡ ላይነቀልም ደደረ፣
ተቃዎሚው፡ ለአንድ አላማ ስለአልተባበረ።
በሀሳብ ተለያይተን፡ እንደ ሰናውር ግንበኛ፣
መቧከስ ሆኗል ስራችን፡ ጠላትን ትተን፡ እኛው በእኛ።
ጊዜ ግን ቆሞ፡ አልጠበቀም፡ ዝምብሎ ፈረጠጠ፣
የኢትዮጵያን ህዝብ፡ በቀን ጎማ እየረገጠ።
የዛሪ ሰባት አመት፡ በወርሃ ጥቅምት፣
አዲስ አበባ ላይ የነበረው፡ የወገን እልቂት።
ዛሪም ይታየኛል፡ በምናቤ ያ! ጩኸት ያ! ዋይታ፣
እናት ከምር በማዘን እንዲያ፡ ደረቷን ስትመታ።
ዓይኔ ላይ ነው አሁንም፡ ያ! ምር አዘንና ለቅሶ፣
የአዲስ አበባ፡ ጎዳና በወገን ደም እርሶ።
ያ! ሰቀቀን የጣር ድምጽ! እንኳን ለኢተዮጵያ ዜጋ፣
ለተመለከተ፡ ባዳንም ቢሆን፡ በፍጹም አይፋቅም ከአይነ ስጋ።
ለነገሩ በእኛ ብቻም አይደለም፡ አየነው ጊዜን በነሱም ሲበር፣
2ቱን የጥፋት መልዕክተኞች፡መለስንና ጳውሎስን በአንድ ባቡር በማሳፈር።
አቶ ጊዜ እንደ ዘበት በወያኔም አልፎ፣
ገላገለን አረመኔ መሪዎቹን ያለእድሜያቸው ቀስፎ

እሮጠ ጊዜ በረረ እንሆ ፈጥኖ ደረሰ፣
ከእኛ ዘንድ  ብቻ ሳይሆን ከእነእሱም ቤት ተለቀሰ።
ወይ ጊዜ!! እንዳላማህ በጠላትም፡ ትደርሳለህ፡
እንዳላመሰግንህ፡ በራሴም ትመጣለህ።
ይሻለኛል ዝም ብዬ ብልህ ጊዜ ሚዛኑ፣
ስትጥልም፡ ሆነ ስታነሳ፡ አድሎ የማታውቅ በመሆኑ።
ስተጥልም፡ ሆነ ስታነሳ፡ አድሎ የማታውቅ በመሆኑ።
ህዳር ወር2005 ዓ.ም
1997ዓ.ም ለተገደሉ ሰማእታት መታሰቢያ ላይ የቀረበ፡